# ደንብ

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ

**ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች፡-** 1KA, 1KA-RA, 1KB-RA, 1KC-RA, 1OE-RA, JFA, JFA-RA, JGA-RB, KLA, KLA-RA

**የሚመለከተው ቢሮ፡-** የት/ቤት ድጋፍ እና ጤናማነት ቢሮ፤ ዋና የትምህርት ኦፊሰር/ሀላፊ

## የተማሪ በትምህርት ላይ መገኘት/ክትትል

I. **ዓላማ**

ከትምህርት መቅረት እንደሚመዘገብ እና በምክንያት የመቅረት ሃላፊነት-ተጠያቂነት

በ*በሜሪላንድ ህግ ድንጋጌ* (COMAR) ላይ በተቀመጡት መስፈርቶች መሰረት ከተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች ጋር የተማሪዎችን የትምህርት ክትትል ለመቆጣጠር እና በትምህርት ላይ የመገኘት ክትትልን የማሻሻል ሂደቶችን ለመዘርዘር።

II. **ትርጓሜ**

*ህጋዊ መቅረት* ማለት በ COMAR 13A.08.01.03 ስር የተጠቀሰው ተማሪ ከት/ቤት የሚቀርበትን ሁኔታ የሚያሳይ ነው።

III. **ቅደም-ተከተል**

ሀ. ሁሉም ት/ቤቶች

1. የት/ቤት ድጋፍ እና ጤናማነት ቢሮ፣ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቢሮዎች እና የውጪ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር፣ መደበኛውን ት/ቤት መምጣት/መከታተል ለመደገፍ የተቀረፀ ቀጣይነት ያለው ማስተካከያዎችን (interventions) ያዘጋጃል እና ይተገብራል።

2. እያንዳንዱ ት/ቤት የራሱን መደበኛ ሂደት በማዘጋጀት የተማሪን ትምህርት መከታተል ይደግፋል። ይህም ስልት መረጃዎችን ይቆጣጠራል፣ የትኩረት ማስተካከያዎችን ያመለክታል፣ እና ማበረታቻዎችን ያካትታል።

3. በፈቃድ መቅረቶች

   በ COMAR ስር ለተጠቀሱ "ህጋዊ መቅረቶችን" MCPS ፈቃድ የሚሰጠው በሚከተለው መንገድ ነው፡-

   ሀ) በቅርብ ቤተሰብ መሞት ምክን

   ለ) የተማሪ ህመም እና የደህንነት ስጋቶች

   የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች በትምህርት ላይ በብቃት

ለመሳተፍ እንዲችሉ አካላዊ፣ ስሜታዊ እና ስነ ልቦናዊ ደህንነት እንደሚያስፈልጋቸው ይገነዘባል። ትምህርት ቤቶች ተማሪው(ዋ) አካላዊ ወይም ስነ ልቦናዊ ደህንነትን በሚደግፉ ተግባራት ላይ ለመሠማራት፥ ወይም በህመም ምክንያት የቀረ(ች) ከሆነ የተማሪው(ዋ)ን መቅረት ምክንያታዊ አድርገው ይቀበላሉ።

(1) በዚህ ደንብ ስር ህጋዊ መቅረትን የሚያሟሉ የደህንነት ተግባራት ማለት መልካም የአካል እና/ወይም የአዕምሮ ጤንነትን የሚደግፉ ፕሮግራሞች እና ቴክኒኮች በመሆን አንድ ተማሪ መመለስ እና ትምህርት መከታተል የሚያስችሉ ናቸው።

(2) አንድ ተማሪ የተደጋገመ ወይም ለረዥም ጊዜ ከትምህርት ቤት የቀረ(ች) ከሆነ፣ ርዕሰ መምህሩ የተማሪው(ዋ)ን ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ የሆነ ተማሪ ፈቃድ ካለው የጤና አጠባበቅ ባለሙያ የቀረ(ች)በትን ምክንያት ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቅ ይችላል። ከጤና አጠባበቅ ባለሙያ የተሰጠ ማስረጃ ከሌለ በተራዘመ የስነ-ልቦና ደህንነትን ምክንያት መቅረታቸውን ለማረጋገጥ ቤተሰብን የሚረዱ የማህበረሰብ ኤጋር ኤጀንሲዎች ወይም የተማሪን መቅረት የሚያውቁ የት/ቤት ሰራተኞች በመመዝገብ ሊረዱ ይችላሉ።

(3) MCPS የት/ቤት እና የማህበራሰብ የባህሪ ጤና ግብዓቶችን በተመለከተ ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦች መረጃ ይሰጣል። በተጨማሪም ይሄ መረጃ ተማሪ የቀረው በማህበራሰብ የባህሪ ጤና ፍላጎት ጋር በተገናኘ እንደሆነ ለሚያሳውቁ ተማሪዎች እና እና/ወይም ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚሰጥ ይሆናል።

ሐ) እርግዝና- ወይም ከልጅ ማሳደግ የሚዛመዱ ሁኔታዎች

(1) ት/ቤቶች እርግዝና- ወይም ከልጅ ማሳደግ የሚዛመዱ ሁኔታዎች ጋር ለሚዛመዱ ሁሉም መቅረቶች ፈቃስ ይሰጣሉ፣ ይሄም የሚያካትተው ምጥ፣ ወሊድ፣ ማገገም፣ እና ቅደመ-ወሊድ እና ድህረ-ወሊድ የህክምና ቀጠሮዎችን ነው፣ የሚያካትተውም –

(ሀ) የተማሪ(ዋ)ው ልጅ ከተወለደ በኋላ ለወላጅነት ተማሪ ቢያንስ ለ 10 ቀናት መቅረት ትችላለች/ይችላል፣

(ለ) ከልጅ ማሳደግ የሚዛመዱ መቅረቶች ወይም የተማሪ ልጅ የህክምና ቀጠሮ፣ ይሄም የሚያካትተው በትምህርት አመት ውስጥ እስከ አራት ቀናት ለሚደርሱ መቅረቶች ት/ቤቱ ከልጁ ፈቃድ ያለው የጤና-አገልግሎት አቅራቢ ማስረጃ መጠየቅ ላይኖርበት ይችላል፤ እና

(ሐ) ማንኛውም ከእርጉዝ ወይም ከልጅ አሳዳጊ ተማሪ ጋር የተገናኘ የህግ ቀጠሮ ምክንያት መቅረት፣ ማለትም ከቤተሰብ የህግ ሂደቶች፣ ይሄም ማደጎን፣ አሳዳጊነትን እና መጎብኘትን ያካትታል።

(2) ትምህርት ቤቶች ለተማሪዋ በእርግዝና ወይም በወሊድ ምክንያት ሆስፒታል ከገባች በኋላ ከተማሪዋ ፈቃድ ካለው የጤና አጠባበቅ ባለሙያ የሚሰጥ ማስረጃ ሊጠይቁ የሚችሉት በሌሎች ሁኔታዎች ሆስፒታል ከሚገቡ ተማሪዎች ሁሉ እንደዚህ አይነት ተመሳሳይ ሰነዶችን የሚጠይቁ ከሆነ ብቻ ነው።

መ) የፍርድ ቤት መጥሪያዎች

ሠ) አደገኛ የአየር ሁኔታ፥ ትርጓሜውም ወደ ትምህርት ቤት እና ከትምህርት ቤት መልስ በሚጓዙበት ጊዜ የተማሪን ጤንነት ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል የአየር ሁኔታ ማለት ነው

ረ) በት/ቤት፣ በአካባቢ የትምህርት ሥርዓት፣ ወይም በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት፣ ተማሪዎችን ከትምህርት ሊያስቀራቸው የሚችል መሆኑን በአካባቢ የት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ወይም በት/ቤት ርዕሰ-መምህር/ተወካይ ተቀባይነት ያለው ወይም የተፈቀደ ሥራ። ርዕሰ-መምህር/ተወካይ ህጋዊ አድርጎ መቀበል ያለበት በተለያዩ ተግባራት ወይም የስራ ሁኔታዎች የተነሳ ከአምስት የትምህርት ቀናት አስቀድሞ ተማሪው(ዋ) ወላጅ/ሞግዚት/ብቃት ያለው ተማሪ ምክንያቱን በጽሑፍ ከጠየቀ ሲሆን ከዚህ ስር የተጠቀሱትን ያካትታል፦

(1) ኮሌጅ ለመጎብኘት እና በኮሌጅ የማስተዋወቂያ ፕሮግራሞች ለመሳተፍ (ገደቡን በሚመለከት የአካባቢውን የተማሪ መመሪያ መጽሔት ይመልከቱ)

(2) ከወደፊት ቀጣሪዎች ጋር ለቃለ-መጠይቅ የተያዘ ቀጠሮ

(3) በቅንጅት የመማር ፕሮግራም ያልተመዘገቡ እና ለአጭር-ጊዜ የሙሉ-ሰአት ሥራ ለተመደቡ ተማሪዎች

ሰ) ኃይማኖታዊ በዓል ለማክበር

ሸ) የሀገራዊ አደጋ

ቀ) ጊዜያዊ መባረር/መታገድ

በ) የመጓጓዣ አገልግሎት እንዲሰጣቸው የተፈቀዳላቸውን ተማሪዎች ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የትራንስፖርት አገልግሎት እንዳይሰጥ የሚያግዱ/የሚከለክሉ ሁኔታዎች በዲስፕሊን ቅጣት ምክንያት ከ MCPS የመጓጓዣ አገልግሎት መታገድን አይጨምርም

(ተ) በት/ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ ወይም ተወካይ ግምት/ምልከታ ከትምህርት ቤት ለመቅረት በቂ/አሳማኝ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ ሌሎች አስቸኳይ/አጣዳፊ ምክንያቶችና ሁኔታዎች

2. ከትምህርት የቀረ(ች)በት ሁኔታ ህጋዊ መሆኑን ወይም ህጋዊ አለመሆኑን ማረጋገጥ

ሀ) ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በተጨማሪ የሆኑትን መቅረቶች እንደ ህጋዊ አድርጎ የመቀበል ዋና ስልጣን የተፈቀደ ነው። እንደአግባቡ ለቤተሰብ ጉዞ ፈቃድ መጠየቅ እንደህጋዊ መቅረት አይቆጠርም።

በርዕሰ-መምህር/ተወካይ ውሳኔ የተማሪ መቅረት ህጋዊ ተደርጎ ሊቆጠር የሚችለው በሚከተሉት ምክንያቶች ተመስርቶ መሆን አለበት፦

(1) በተማሪው(ዋ) መቅረት ምክንያት በትምህርቱ(ቷ) ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ ለመቀነስ የማካካሻ ሥራ ሊኖር እንደሚችል የተማሪን የመቅረት ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ከተማሪው(ዋ) መምህር/መምህራን አስተያየት ከተሰጠ

(2) ተማሪው(ዋ) እስከ ዛሬ የተከማቸበ(ባ)ት ህጋዊ እና ህገ-ወጥ መቅረቶች ብዛት

(3) መቅረት ያስፈለገበት ዓላማ ወይም ልዩ ጥቅም

(4) የቀረ(ች)በት ጊዜ ብዛት

ሐ) በፈቃድ መቅረቶች ውስጥ ውሳኔ ለማግኘት፣ ማሳወቂያ እና የፈቃድ ጥያቄ ከመቅረት በፊት መቅረብ አለበት።

4. ት/ቤት ሙሉ ጊዜ ት/ቤት ለተከታተሉ ሽልማት መስጠት ቢያስፈልግ በኃይማኖታዊ ምክንያት ለመቅረት የተፈቀደላቸውን ተማሪዎች ከመሸለም አያግድም።

5. ከት/ቤት መቅረት ጋር የተያያዙ መንስኤዎችን ማረጋገጥ

ሀ) ለሪፖርት አቀራረብ እንዲያመች፣ የሞንጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) *በሜሪላንድ የተማሪ ሪኮርድ ስርዓት መምሪያ* መቅረት የሚለውን ቃል "የቀረባቸው/ችባቸው ቀናት" የሚል ትርጓሜ ተሰጥቶታል።

ለ) የሜሪላንድ የተማሪ ሪኮርድ አያያዝ መምሪያ ለማመሣከሪያነት ከዚህ ጋር አባሪ ተደርጓል።

ሐ) ተማሪ በአካል መማሪያ ክፍል በማይገኝበት/በማትገኝበት ጊዜ፥ ነገር ግን በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ቀጥታ ቁጥጥር እስከተደረገ ድረስ ለስቴት እና ለአካባቢ ሪፖርት አላማዎች እንደተገኙ ተደርጎ ይቆጠራል፣ ይሄም ቢሆን ግን በመማሪያ ክፍል ውስጥ አለመገኘታቸውን ለማረጋገጥ በመምህር አማካይነት ቀሪ ተብሎ ይመዘገባል። በስቴት እና በአካባቢ ሪፖርቶች ላይ በትክክል መመዝገቡን ለማረጋገጥ እንዲረዳ የቀሪ ተቆጣጣሪ ጸሐፊ ተግባራዊ የሆነ መለያ ኮድ ይመድባል/ትመድባለች። በዚህ ብቻ ባይወሰንም ይህን የመሳሰለ የመቅረት ምሳሌዎች፡-

(1) በ MCPS የመስክ ትምህርት ፕሮግራሞች በበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ለመስጠት

(2) የ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የአትሌቲክስ ተሳትፎ

(3) በተማሪ አመራርነት ምክንያት ለሚያጋጥም ተግባር

(4) የመስክ ጉዞ

(5) የጤና አገልግሎት ክፍል ጉብኝት

(6) መካከለኛ/መሸጋገሪያ የትምህርት አገልግሎቶች

(7) ከት/ቤት መታገድ

መ) በረዥም ጊዜ ጉዞ ምክንያት ወይም ምክንያቱ ሳይገለጽ ከ 15 ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ በወላጅ/ሞግዚት አማካይነት ከት/ቤት የቀሩ ተማሪዎች ከት/ቤት እንደለቀቁ ስለሚቆጠር፣ተማሪው(ዋ) ከት/ቤት እንደለቀቀ(ች) ለወላጅ/ሞግዚት ይገለፃል እናም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሚገምተው ወላጅ/ሞግዚት ተማሪው(ዋ) ከሄዱበት ቦታ ትምህርት የማስቀጠል ኃላፊነታቸውን እንደሚያሟሉ ተደርጎ ይታሰባል።

ሠ) ተማሪው(ዋ) ወደ ት/ቤት በተመለሰ(ች) በሦስት ቀን ውስጥ ከወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ከሆነ(ች) ተማሪ የሚቀርብ የእያንዳንዱን የቀረ(ች)በትን ምክንያት የሚገልጽ የጽሑፍ ማስረጃ ያስፈልጋል።

ረ) አርፍዶ ስለመምጣት ወይም ቀደም ብሎ የመውጣት ፈቃድ ጥያቄዎች በወላጅ/ሞግዚት መረጋገጥ አለባቸው።

ሰ) “ብቁ ተማሪ” ምን ማለት እንደሆነ "MCPS ደንብ JEA-RB" ላይ ተገልጿል፣ *የተማሪዎች ምዝገባ*። ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ ስለመቅረት ማስታወሻ ማቅረብ እና አርፍዶ ስለመምጣት እንዲሁም በትምህርት ሠዓት ቀድሞ ስለመውጣት ጉዳይ ኃላፊነት መውሰድ ይኖርበ(ባ)ታል። ርዕሰ መምህር/ተወካይ ብቁ ስለሆነ(ች) ተማሪ የሚከተለውን በጽሑፍ ለወላጅ/አሳዳጊ የመግለጽ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት።

(1) ብቃት ያላቸው ተማሪዎች የቀሩበትን ምክንያት ራሳቸው በጽሑፍ ለማቅረብ ይችላሉ።

(2) እድሜው(ዋ) የሚፈቅድ ተማሪ ላይም ሕገ-ወጥ ከትምህርት የመቅረት ሁኔታን አስተዳደራዊ ክትትል ይደረጋል። በተጨማሪ ተማሪው(ዋ) ከወላጅ/ሞግዚት ጋር በጥገኝነት የሚኖር/የምትኖር ከሆነ ሳይፈቀድ የመቅረቱ(ቷ) ሁኔታ ለወላጅ/ለአሳዳጊ ይገለፃል።

6. *ቀሪዎችን መመዝገብ*

ሀ) እያንዳንዱ የክፍል አስተማሪ የተማሪዎችን ክትትል የመመዝገብ ኃላፊነት አለበ(ባ)ት። መምህራን የተማሪዎችን መገኘት/አለመገኘት በቀጥታ በኦንላይን የመቆጣጠሪያ ዘዴ ይመዘግባሉ። ስርዓቱ (System) የተመዘገበበትን ቀን፣ ሠዓት፣ እና መረጃ መዝጋቢውን ሰው ይገልጻል።

ለ) የኤሌክትሮኒክስ መመዝገቢያ ስርዓቱን መጠቀም በማይቻልበት ጊዜ፣የወረቀት መዝገብ ስራ ላይ ይውላል። እነኚህ መረጃዎች/ዶኩሜንቶች የትምህርት ዓመቱ እስከሚያልቅ በት/ቤት ውስጥ ይቀመጣሉ። በወረቀት ቅፅ የተያዙ ሰነዶች ለኦዲት አገልግሎት በያዝነው የትምህርት ዘመን መጨረሻ ለሦስት ተጨማሪ ዓመታት እንዲቆዩ ወደ ማዕከላዊ የሪከርድ ቋት ይላካሉ።

ሐ) የእያንዳንዱ ተማሪ ዕለታዊ በትምህርት ላይ የመገኘት ሁኔታ በተማሪ መረጃ ስርዓቶች ቢሮ በኤሌክትሮኒክስ ሪኮርድ ይያዛል።

7. ከትምህርት መቅረትን መቆጣጠር

   ሀ) ተማሪው(ዋ) የቀረ(ች)ባቸው ቀኖች በጠቅላላ (በፈቃድ የሆኑትና ያለፈቃድ የቀረ(ች)ባቸው) በሪፖርት ካርድ ላይ ሪፖርት ይገለፃሉ።

   ለ) ርዕሰ መምህር/ተወካይ ከት/ቤት ባልደረቦች ጋር በመተባበር፣ ከት/ቤት ስለመቅረት ለመከታተል የሚያስችል ሥርዓት በመመስረት በየዓመቱ ጁላይ 1 ላይ እንዲጸድቅ ለሚመለከተው የት/ቤቶች ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት ያቀርባል፣ እና ለወላጆች/ሞግዚቶች እና ለተማሪዎች በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ የጸደቀው የመቆጣጠሪያ ሥርአት ይሰጣቸዋል።

ለ. አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች (መዋለ ህጻናትን ይጨምራል)

1. በትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ ልጃቸው በማንኛውም ቀን በምንም ምክንያት ከት/ቤት የሚቀር/የምትቀር ከሆነ ለት/ቤት እንዲያሳውቁ የኤለመንተሪ ትምህርት ቤት ርዕሰመምህራን/ተወካዮች ወላጆችን/ተወካዮችን ይጠይቃሉ።

2. እስከተቻለ ድረስ፣ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት እድሜ ክልል የሚገኙ ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች ልጃቸው ከት/ቤት እንደሚቀሩ አስቀድመው ካላሳወቁ በስተቀር በ12፡00 ሠዓት እኩለ ቀን ላይ በእያንዳንዱ መጀመሪያ በሚቀሩበት ቀን ይነገራቸዋል።

3. በፈቃድም ሆነ ያለፍቃድ ከመጠን በላይ መቅረት የሚያበዙ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች እና/ወይም አርፋጆች አግባብነት ወዳለው ማስተካከያ ተግባር እንዲተላለፉ ሊደረግ ይችላል። በርዕሰ መምህሩ/ሯ ወይም በእርሱ/ሷ ተወካይ ፈቃድ፣ ደጋግሞ የመቅረት አዝማሚያ ያሳዩ ተማሪዎች በት/ቤት በመደበኛነት መገኘትን ለመጨመር የተቀረጹ ከበድ ያለ የማስተካከያ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ ወደ ተገቢው ሠራተኛ ወይም ከት/ቤት ውጭ ወደ ሚገኙ ሌሎች ኤጀንሲዎች ሊላኩ ይችላሉ።

ሐ. ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች

በህጋዊም ሆነ ህጋዊ ባልሆነ ምክንያት ከመጠን በላይ መቅረት የሚያበዙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች እና/ወይም አርፋጆች አግባብነት ወዳለው ማስተካከያ ትግበራ እንዲተላለፉ ሊደረግ ይችላል። በርዕሰ መምህሩ/ሯ ወይም በእርሱ/ሷ ተወካይ ፈቃድ፣ ደጋግሞ የመቅረት አዝማሚያ ያሳዩ ተማሪዎች በት/ቤት በመደበኛነት መገኘትን ለማዘውተር የተቀረጹ ከበድ ያሉ የማስተካከያ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ ወደ ተገቢው ሠራተኛ ወይም ከት/ቤት ውጭ ወደ ሚገኙ ሌሎች ኤጀንሲዎች ሊላኩ ይችላሉ። አምስት ቀኖች ወይም ከዚያ በላይ ከት/ቤት ያለፈቃድ የቀሩ ተማሪዎች ከት/ቤት ቀሪ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይሰጣቸዋል።

መ. ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች

1. በህጋዊም ሆነ ህጋዊ ባልሆነ ምክንያት ከመጠን በላይ መቅረት የሚያበዙ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች ተገቢ ወደ ሆነው ማስተካከያ እንዲሄዱ ሊደረግ ይችላል። የት/ቤት ካውንስለር ተማሪዎች የቀሩበትን ምክንያት ለማረጋገጥ እና ተገቢ የሆነ ማስተካከያ እርምጃ ለመወሰን ከተማሪው(ዋ) እና ከወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ምክክር ያደርጋል/ታደርጋለች።

2. በርዕሰ መምህሩ/ሯ ወይም በእርሱ/ሷ ተወካይ ፈቃድ፣ ደጋግሞ የመቅረት አዝማሚያ ያሳዩ

ተማሪዎች በት/ቤት በመደበኛነት መገኘትን ለመጨመር የተቀረፁ ከበድ ያለ ማስተካከያ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማድረግ ወደ ተገቢው ሠራተኛ ወይም ከት/ቤት ውጭ ወደሚገኙ ሌሎች ኤጀንሲዎች ሊላኩ ይችላሉ።

3. የትምህርት ቤት ካውንስለሮች/የአስተዳደር ቡድኖች ትምህርት ቤት የመከታተል-የመከታተል/የመገኘት ማስተካከያ ዕቅድን/Attendance Intervention Plan (AIP) ለተማሪ ትምህርት የመከታተል ማሻሻያ አድርገው ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

   ሀ) እያንዳንዱ ተማሪ ስለሚወስዳቸው ኮርሶች MCPS Form 560-26B ቅጽ በመጠቀም የሚዘጋጀው ትምህርት የመከታተል/የመገኘት ማስተካከያ ዕቅድ/Attendance Intervention Plan (AIP)፣ የመከታተል/የመገኘት ማስተካከያ ዕቅድ፣ *ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ብቻ/Attendance Intervention Plan, High School Students Only* የተማሪን የትምህርት ክትትል እና ትምህርታዊ ሥራ ስለማሻሻል ተማሪው(ዋ) እና/ወይም ሠራተኛ አማካይነት መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች እና ስትራቴጂዎች በቅፁ ላይ ተቀምጠዋል።

   ለ) ርዕሰ መምህር AIP ከመረመረ(ች) በኋላ ይፈርምበታል/ትፈርምበታለች።

   ሐ) AIP በመተግበር ላይ እያለ፣ በ AIP ምክንያት የተገኘውን መሻሻል ለመወሰን ርዕሰ መምህሩ በሴሚስተሩ ውስጥ በሙሉ የተማሪው(ዋ)ን ትምህርት ላይ የመገኘት ግምገማ ይመራል።

ሠ. MCPS ደንብ KLA-RA፣ *ከማህበረሰቡ ለሚነሱ ጥያቄዎች እና አቤቱታዎች ምላሽ መስጠት*፣ የርዕሰ-መምህር/ተወካይ ውሳኔ ላይ አቤቱታ የማስቀመጫ አካሄዶችን ያስቀምጣል።

***ተዛማጅ ምንጮች፡-*** አባሪ የሜሪላንድ ኮድ፣ የትምህርት አንቀፅ፣ §7-301.1፤ *የሜሪላንድ መተዳደሪያ ደንቦች*§13A.03.02.08B(4) እና §13A.08.01.01–07፤ MCPS *የሀይማኖት ልዩነቶችን ለማክበር መመሪያዎች፤ የተማሪ መብቶች እና ሀላፊነቶች መመሪያ፤ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪ ስነምግባር ደንብ*

***የዚህ ደንብ ታሪክ፡-*** የቀድሞ ደንብ ቁጥር 515-1፣ ሴፕቴምበር 12, 1980 (መመሪያው ተሻሽሏል)፣ ዲሰምበር 1986 ተሻሽሏል፤ አክቶበር 28, 1993 ተሻሽሏል፤ ኦገስት 19, 1997 ተሻሽሏል፤ ኖቨምበር 3, 2005 ተሻሽሏል፤ ሜይ 12, 2010 ተሻሽሏል፤ አክቶበር 7, 2013 ተሻሽሏል፤ ፌብሩወሪ 4, 2014 ተሻሽሏል፤ ሴፕቴምበር 11, 2014 ተሻሽሏል፤ ኦገስት 6, 2015 ተሻሽሏል፤ ፌብሩወሪ 9, 2018 ተሻሽሏል፤ አክቶበር 8, 2019 ተሻሽሏል፤ ኤፕሪል 28, 2022 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/ መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of Academic Officer<br>Resolution and Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 208, Rockville, MD 20850<br>240-740-3230<br>RACU@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2100, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

*ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org